# በኢኦተቤ የሆሳዕና ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

## መንፈሣዊ ማኅበር

## የ!)08 ዓ.ም ዕቅድ፣

ነሐሴ !)08 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>፣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ 1 አምላክ አሜን!!!

በኢኦተቤ የማኅበረ ሆሳዕና ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ የ!)08 ዓ.ም ዕቅድ

ልዑል እግዚአብሔር ቢፈቅድና ብንኖር በ!)08 ዓ.ም ቀጥሎ የተዘረዘሩ ተግባራትን እናከናውናለን ብለን ዕቅድ አዘጋጅተናል። ዕቅዱ የተለያየ አርዕስተ ጉዳዮችን በዝርዝር ያካተተ ሲሆን ይዘቱም፣ መግቢያ፣ ዓላማ፣ አስፈላጊነትና ወሰን፣ ዋናዋና እና ዝርዝር ተግባራት እንዲሁም የአፈጻፀም ክትትል ሥልትና ማጠቃለያ የያዘ ነው። ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል።

የዕቅዱ መነሻ ተደርጎ የተወሰደው ለሀገረ ስብከቱ ቀርቦ በፀደቀው የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በተቀመጠው የማህበሩ ዓላማና ተግባር አስመልክቶ እንዲሁም የተዘረዘሩ ዋናዋና ጉዳዮች ናቸው፤ እነዚህም፣

(1) በአገረ ስብከቱ የሚከናወኑ መንፈሣዊ ተግባራት ይሳኩ ዘንድ በሀሳብ፣ በጉልበትና በገንዘብ መደገፍ፣
(2) የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ገቢ ማሰባሰብና ለቤተ- ክርስቲያን ሁለንተናዊ አገልግሎት የሚውሉ ንዋያተ ቅድሳትን ማቅረብ፣
(3) በየደረጃው ለሚገኙ አገልጋዮች እገዛና ድጋፍ ማድረግ (በአቅም ግንባታ እና በፋይናንስ/ገንዘብ)፣

(4) ትምህርተ- ወንጌልን ለማስፋፋት ይረዳ ዘንድ የኤሌክትሮኒክስና ኅትመት ሚዲያዎችን እንዲሁም ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ተግባራዊ ማድረግ፣

(5) በየአካባቢው በሚነገረው ቋንቋ የስብከት፣ የማስተማርና የዝማሬ አገልግሎት የሚሰጡ ወጣቶችና ማፍራትና መደገፍ፣ ሲሆኑ

እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት ከማኅበሩ ሥራ አስፈጻሚ፣ ከአባላትና ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመሆን አሁን በተጨባጭ ከአለንበት ሁኔታ ተነስተን ልንደርስባቸው የሚገቡ ውጤቶችን ለማምጣት የትግበራ ሂደቶችና የአፈጻፀም ክትትል የሚደረግባቸው ስልቶች ተቀምጠዋል። ዕቅዱ በአጭር፣ በመካከለኛና በረዥም ጊዜ ተለይቶ እንዲቀመጥ ተደርጓል።

አሁናዊ/ነባራዊ ሁኔታዎች ሲቃኙ የታዩ ጥንካሬዎች፣ ክፍተቶችና ያጋጠሙ ችግሮች በአጭሩ

ሀ) በጥንካሬ፡

- ወርሃዊ መርሐ- ግብር ሳይቆራረጥ ማካሄድ መቻሉ፣
- የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መጽደቁ፣
- ዓመታዊ ጉባዔ መካሄዱ፣
- ለቅዳሴ አገልገሎት የሚውሉ ግብዓቶች ግዥ ተፈጽሞ መላኩ፣
- የመንፈሣዊ ጉዞ መርሐ- ግብር መከናወኑ፣
- ለአንድ ገጠር ቤተ- ክርስቲያን ገቢ ማሰባሰቢያ ጉባዔ ሲካሄድ ለአገልጋዮች ክፍያ መፈፀሙ፣
- የሁለት አገልጋይ ካህናት ቅጥር መፈፀሙ (ማህበራችን ወርሐዊ ደመወዛቸውን በማህበራችን የሚፈፀም መሆኑ እንዲሁም ለአንድ አገልጋይ ካህን የደመወዝ ድጎማ መደረጉ)፣

ዋናዋናዎቹ ናቸው።

ለ) የታዩ ክፍተቶች፡

- የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ወደሙሉ ትግበራ መግባት አለመቻሉ፣
- አባላትን ከማፍራት አንጻር ያለው እንቅስቃሴ ክፍተት የታየበት መሆኑ፣
- የአባላት በየወሩ በመገናኘት ረገድ የመቀዛቀዝ ሁኔታ መኖሩ፣
- ሥራዎች በተወሰኑ ግለሰቦች ላይ ብቻ እየተንጠለጠሉ መሆኑ፣
- ጉባዔ ለመዘርጋት ቢታሰብም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያች አካሄድ አለመኖሩ፣
- የግንኙነት መጓደል፣
- የመሰብሰቢያ/የመገናኛ ሥፍራ/ጽ/ቤት አለመኖር፣
- ማህበሩ በራስ አቅም ወደተሟላ አገልግሎት ለመሸጋገር የሚያስችል አሰራር

እንዳይከተል በአገረ- ስብከቱ በኩል ሊደረግ የሚገባው ድጋፍ በሚጠበቀው ልክ

አለመሆኑ፣

የሚሉት ዋናዋናዎቹ ናቸው

የ!)08 ዓ.ም ዕቅድ፣

ዋና ተግባር አንድ፡ ሁለንተናዊ ድጋፍ ማድረግ

ዐቢይ ተግባር 1.1. በሀሳብ፣ በጉልበትና በገንዘብ መደገፍ፣

ዝርዝር ተግባራት፡

1.1.1. የተለያዩ ሀብቶችን (የሰው አቅም/ዕውቀትና ክህሎት፣ ፋይናንስ እና ቁሳቁስ) ምንጫቸውን መለየት፣ ማሰባሰብና ለአገልግሎት ማደራጀት፣

✝ በተለያየ አግባብ ሙያና ዕውቀት ያላቸውን የማህበሩን አባላትና ደጋፊዎች እንደየአቅማቸው አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ጥሪ ማስተላለፍና ምዝገባ በማካሄድ፣ ሥራ መስጠት፣

✝ የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስልቶችን በመንደፍ ገንዘብ ማሰባሰብ፣

✝ የተሰበሰበውን ገንዘብ የፋይናንስ አሠራርን ተከትሎ በህጋዊ መንገድ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል መከታተል፣

✝ ከአገር ውጪ ያሉ የሆሣዕናና አካባቢዋ ልጆች የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ በማኅበራዊ ትስስር ገፆች ተከታታይና ጠንካራ የፕሮሞሽን ሥራ መስራት፣

✝ አዳዲስ አባላትን በማፍራት ረገድ በቂ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ

ዋና ተግባር ሁለት፡ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን መለየትና መጠቀም፤

2.1.1. የአባላትን መዋጮ እና ቃል የተገቡ ክፍያዎችን በአግባቡ ተከታትሎ እንዲሰበሰብ ማድረግ፣

2.1.2. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪን በየዓመቱና ሌሎች ጉባዔዎችን ደግሞ በዓመት ሁለት ጊዜ በተጠናከረ ሁኔታ(አንዱን በአዲስ አበባ አንዱን ደግሞ በሆሣዕና እንዲካሄድ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ፣ በየጉባዔዎቹም ለሽያጭ የሚቀርቡ ቁሣቁሶችን ማቅረብ ሌሎች መንገዶችን በመከተል (እንደ አብነት ዘጋቢ ቪዲዮዎችን ማራኪ በሆነ ሁኔታ አዘጋጅቶ ለዕይታ እንዲበቁ በሽያጭ ማቅረብ) ገቢማሰባሰብ፣

2.1.3. በዓመቱ ውስጥ ከሦስት እስከ አራት የሚደርሱ መንፈሣዊ ጉዞዎችን ማዘጋጀት፣

2.1.4. የተለያዩ ድርጅቶችን በማወያየት ስፖንሰር እንዲያደርጉ ማፈላለግ፣

2.1.5. ከአዲስ አበባ አገረ-ስብከት ጋር በመነጋገር በየአጥቢያ ቤተ- ክርስቲያን ገቢ የሚገኙና ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንዋያተ ቅድሳት በማሰባሰብ ወደገጠር ዐቢያተ- ክርስቲያን አገልግሎት ላይ እንዲውሉ መላክ፣

2.1.6. በየአድባራቱ/አጥቢያ ቤተ- ክርስቲያን አካባቢ በኅብረተሰቡ ተሣትፎ ሊለሙ የሚችሉና ገቢ የሚያስገኙ ፕሮጀክቶችን በዳሰሣ ጥናት በመለየት የአካባቢውን ኅብረተሰብ በማሳተፍ ቁምር በአጭር ጊዜ ወደሥራ እንዲገቡ በማድረግ ራሳቸውን ማስቻል፣(የፕሮጀክቱ ዓይነት፣ የሚያስፈልግ በጀትና የፋይናንስ ምንጭ፣ ወዘተ... ያካተተ ዝርዝር የድርጊት መርሐ- ግብር ይዘጋጃል)

ዋና ተግባር ሦስት፣ አራትና አምስት፡ አገልጋዮችን ማፍራት፣ እገዛና ድጋፍ ማድረግ

3.1.1. አገልግሎትን በተመለከተ አሁናዊ ሁኔታዎችን በማጥናት የነባር አገልጋዮችን አቅም የማጎልበትና ተተኪዎችን ለማፍራት የሚያስችሉ ሥራዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት፣

3.1.2. በሰንበት ትምህርት ቤቶች አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ወጣቶችን ወደወንጌል አገልግሎት እንዲገቡ ሁለንተናዊ እገዛ ማድረግ ላይ ጠንካራ ሥራ መስራት፣

3.1.3. ልብሰ-ተክህኖና የተለያዩ ንዋያተ ቅድሳት ሊሟሉላቸው የሚገቡትን በአግባቡ በመለየት እንደየቅደም ተከተላቸው በተቻለ አቅም ወቅታዊ የሆነ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፣

ሌሎች ተግባራት፡

- የተለያዩ የክትትልና ድጋፍ ሥልቶችን በመጠቀም የተግባራት አፈጻፀምን በመፈተሽ ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፣
- ከአገረ ስብከቱ ሊቀ-ጳጳስ ጋር ተከታታይ ውይይቶችን ማካሄድ፣
- የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴን ዐቅም ማጠናከር፣
- ለሥራ አስፈጻሚው የመገናኛ ቢሮ ማፈላለግ/መከራየት፣
- በሆሳዕና ንዑስ ኮሚቴ ማደራጀት፣ ማጠናከርና ወደሥራ ማስገባት፣
- የውስጥና የውጪ ግንኙነት በተመለከተ ተከታታይነት ያለው ሥራ እንዲከናወን ልዩ ትኩረት መስጠት፣
- የማህበሩን ህጋዊነት በተሟላ ሁኔታ ማረጋገጥ፣
- የአባላት ተሳትፎን ማሳደግ፣
- ያረጁና ዕድሳት ለሚያስፈልጋቸው የገጠር አቢያተ- ክርስቲያን ድጋፍ እንዲደረግ መስራት፣
- በአባላት መካከል ማህበራዊ ግንኙነት የሚፈጠርበትና የሚጠናከርበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣